## ሞረሽ ወገኔ (ብሪታኒያ)
## Moresh Wogenie (UK)

# የፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ ዕልፈተሕይወት
# 16ኛው መታሰቢያ በዓል በለንደን።

ትናንት ዕሁድ ግንቦት ፱ ቀን ፪ሺ፯ ዓም፣ ከስአት በኋላ፣ ለንደን በሚገኘው የኢትዮጱያ ማህበረሰብ አደራሽ ብዙ ኢትዬጵያውያን በተገኙበት፣ የጀግናው፣ የሊቁ፣ የፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ፣ 16ኛው አመት በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ዋለ።

በቦታው የተገኙ የቅርብ ወዳጃቸው፣ የንጉሳውያን ቤተሰብ አባል የሆኑ ወይዘሮ፣ አንድ የቀድሞ ተማሪአቸው የነበሩ ሃኪም፣ አንድ ታካሚአቸው የነበሩ ሕመምተኛ፣ ስለውዱ ፕሮፌሰር ያላቸውን ት ዝ ታና ምስጋና ለተሰብሳቢዉ ተናግረዋል። አንድ ስለፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ፣ በኢትዬጵያ ከታተመ አማርኛ መጽሐፍ ከሰፈሩት ሃሳቦች በአጭሩ ቀርቦአል። ከዚያም ሶስት ግጥሞች በሁለት ገጣሚዎች ቀርበው፣ በቀረበው ሁሉ ውይይት ተደርጎበት፣ አስተያየት ተሰጥቶበት፣ የመዘከሪያው ስብሰባ ከምሽቱ አንድ ሰዐት ተጠናቋል።

በስብሰባው ከቀረቡት ሃሳቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል። ፩ኛ/ የፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ ማስታወሻ ፋውንዴሽን እንዲቋቋም፤ ፪ኛ/ እንደፕሮፌሰር አሥራት፣ ለሃገር፣ ለወገን፣ ሲታገሉ ሕይወታቸው በግፍ ላለፈ፣ እንደ አሰፋ ማሩ ዓይነት ኢትዮጵያውያን ሁሉ በዚህቀን እንድናስታውሳቸው፤ ፫ኛ/ ይህን የዘመናችን ጀግኖች ማስታወሻ ቀን ኢትዬጵያውያን በአንድነትና በቋሚነት እንድናከብረው አስፈላጊው ሁሉ ዝግጅት እንዲደረግ የሚሉ ናቸው።

በቀረቡት ሃሳቦችና በተደረገው ውይይት ጎልቶ የቀረበው የፕሮፌሰር አሥራት መንፈስ ጠንካራነት፣ ሃገር ወዳድነት፣ ሰው አክባሪነትና፣ የሃይማኖት ፅናት፣ ከልጅነት እስከ እውቀት ለትምህርትና ለሙያዊ ተግባር ያሳዩትንና የነበራቸውን ከፍተኛና ጠንካራ አያያዝ ያካትታል።

ፕሮፌሰር አሥራት ከ30 አመት በላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባበረከቱት የሕክምና አገልግሎት ብዙ ሕዝብ በመርዳት ሃገራዊና አለምአቀፋዊ ዕውቅና አግኝተዋል። እሳቸው ግን በሀሰት ተከሰው ወደወያኔ ወህኒቤት ከተወረወሩ በኋላ፣ ታመው፣ ሕክምና ተከልክለው፣ ከተዳከሙ በኋላ፣ ታክመው ሊድኑ የማይችሉበት ደረጃ ሲደርሱ፣ውጭ ሃገር ሄደው፣ እንዲታከሙ፣ ከሃገር እንዲወጡ በማድረግ፣ በውጭ ሃገር ሕይወታቸው አልፎአል። ይህን የወያኔ ግፍ፣ አሁን ያለዉና፣ መጭው ትውልድም እንዲአስታውሰው፣ ይህ ቀን የቆራጡ ኢትዮጵያዊ የፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ መዘከሪያ ቀን ሆኖ በየአመቱ ይከበራል። በመጭው አመት ይህን ቀን በበለጠና በስፋ መልኩ ለሃገራቸውና ለወገናቸው መብት፣ ለእኩልነትና ፣ ለአንድነት ሕይወታቸውን ላሳለፉ ሁሉ በማስታወሻነት ይዘከራል።

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃልኪዳን ነው፤
ኢትዮጵያ በነፃነትና፣ በእኩልነትና፣ በአንድነት፣ ለዘላለም ትኑር።